# የደንና ብዝኀ ሕይወት ጥበቃ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን*

**በዐለማየሁ ዋሴ እሸቴ****


## ABSTARCT

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church (EOTC) has a long history of conservation of forest resources, which usually surround churches. Although the main purpose of churches is as places for worship, burials, meditation and religious festivals, they also provide valuable, often unique, and secured habitats for plants and animals, and green spaces for people.

In the northern highlands of Ethiopia, patchy remnants of age-old Afromontane forests are found mainly around EOTC churches and monasteries. Forests in other areas have been completely destroyed and converted into farms and grazing lands over the centuries. Hence, when a traveler sees a patch of indigenous age-old trees in the northern highlands of Ethiopia, he/she can be sure that there is an Orthodox Church in the middle. They are visible from a great distance, with a majestic appearance, usually situated on small hills "overlooking" the surrounding villages. The local people call these churches with their surrounding trees:s: "*debr*" or "*geddam*". "*Debr*" or "*Geddam*" are designations for holy places, and constitute religiously as well as socially respected powerful institutions. These church forests did not survive by mere chance, rather it was by the patriotic conservation efforts of church members, with their strong theological and biblical justification.

Pilot studies suggest that church forests are relics of ancient and largely lost forest eco-systems, which constitute hotspots of biodiversity for indigenous species, and therefore could serve as priority areas for in-situ conservation, while being maintained as prestigious religious sites. Despite their potential role for conservation and restoration, these forests are currently facing a number of ecological and social challenges which ultimately threaten their survival.


* በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ለናሙና ከተመረጡት ፳፰ አድባራትና ገዳማት የተፈጥሮ ደኖች መነሻ ጥናት የተወሰደ

* *Dr Alemayehu Wassie. Production Ecologist and Resource Conservationist. Gafat Endowment.

## ፩. መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችን በሥነ ጥበብ፣ በታሪክ፣ በማኅበራዊ፣ በአስተዳደራዊ ዘርፎች ልማትና ዕድገት ያበረከተችው አስተዋጽኦ የሚታወቅና ተደጋግሞ የተገለጸ ነው። ይኹን እንጂ ከዚህ በተጨማሪ ለሀገሪቱ የደንና ብዝኀ ሕይወት ሀብት ጥበቃ ያበረከተችውና እያበረከተች ያለው አስተዋጽኦ ብዙም የሚታወቅና ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ አይደለም።

ቤተክርስቲያኗ ጥልቅ የኾነ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ክብካቤ አስተምህሮ (Eco theology) ያላት ተቋም ናት። ይኽ አስተምህሮ ለዘመናት የዘለቀና በደን፣ በብዝኀ ሕይወትና ዘረ መል (genetic) ሀብት ጥበቃ በኩል ስኬትን ያስመዘገበ መኾኑን ሣይንሳዊ ጥናቶች ይጠቁማሉ።[1,2]

በዘመናችን ከዐዲስ አበባ ወደ ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ያቀና ተጓዥ የተፈጥሮ ደኖች ተጠብቀው የሚያየው በአብዛኛው በአድባራትና ገዳማት ዙርያ ነው። በአንድ ወቅት ለምለምና ማራኪ የደን ልባስ የነበረው መልክዐ ምድር በአስደንጋጭ ኹኔታ ተራቁቶ ቅሪት የተፈጥሮ ደኖችን በአድባራትና ገዳማት ዙርያ ብቻ ተበታትነው ለሚያይ ተጓዥ አግራሞትን መፍጠሩና የተደሞ ጥያቄዎችን ማጫሩ አይቀርም። እንዴት እነዚህ ብቻ ሊተርፉ ቻሉ? ማን ጠበቃቸው? በውስጣቸው ምን ይዘዋል? ወደፊትስ በዚህ መልኩ ይቀጥሉ ይኾን? እያለ ማሰላሰሉ አይቀርም።






*ምሥል ፩. ደብረ ታቦር ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው ዮኖኅተ ገነት ደብረ ሲና ማርያም ቅሪት የተፈጥሮ ደን*

## ፪. የአድባራትና ገዳማት ደኖች እንዴት ተጠበቁ?

እነዚህ ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች በአጋጣሚ የተረፉ ሳይኾን በቤተ ክርስቲያኗ ቀደምት ሊቃውንት ሃይማኖታዊ አስተምህሮ (Eco theology) እና በደጋግ አባቶችና እናቶች ልዩ አክብሮትና መስዋዕትነት ነው። ከነዚህ መሠረታዊ አስተምህሮዎች መካከል ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያኽል፡-

---

[1] Alemayehu Wassie, *Opportunities, Constraints and Prospects of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church Forests in Conserving Forest resources: The case of churches in South Gondar, Northern Ethiopia*. (MSc Thesis SLU, Sweden, 2002).

[2]. Alemayehu Wassie, *Ethiopian Orthodox Church Forests: Opportunities and challenges for Restoration*. (PhD Thesis: Wagningen University the Netherlands,2007).

*ቤተ ክርስቲያን የገነት ምሳሌ ናት፦* መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገነት በኦሪት ዘፍጥረት እንዲህ ይላል፤

> *«እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በኤደን ገነትን ተከለ .... እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፣ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ...»*[3]

ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንደ ገነትም ኹሉ ለማየት ደስ በሚያሰኙ፣ ለመብላትም መልካም በኾኑ ዕፅዋት ሊሸፈኑ ስለሚገባ፤

*የመጀመሪያው የአምላክ ትእዛዝ፦* ለመጀመሪያው ሰው አዳም የተሰጠው የመጀመሪያ ትእዛዝና መመሪያ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ነው፡፡ በኦሪት ዘፍጥረት እንዲህ ይላል፤

> *«እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው፡፡»*[4]

*ያበጃትም* ዘንድ ማለት ያለማት፣ ያሣምራት ዘንድ ሲኾን *ይጠብቃትም* ዘንድ ማለት እንዳትጎሳቆል ይንከባከባት፣ ይጠብቃት ዘንድ ማለት ነው፡፡ ስለኾነም ሲኾን መላ ምድሪቱን ያለበለዚያ ደግሞ ቢያንስ በቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ የሰው ልጅ ተፈጥሮን በመንከባከብና በማሳመር ሓላፊነቱን በመወጣት የአምላኩ ታዛዥ መኾን እንደሚገባው ለማሳየት ነው፡፡

*የሰውን ልጅ መውደቅና መነሣትን ለመዘከር፦* የሰው ልጅ የመጀመሪያ ውድቀት በዕፀ (ዕፀ በለስ) በመብላት እንደተጀመረ ኹሉ የመዳን ተስፋውም በዕፅ (ዕፀ መስቀል) በመፈጸሙ የዕፅዋት መኖር ክርስቲያኖች ኹልጊዜ የመውደቃቸውንና የመዳናቸውን ነገር የሚያስታውሱባቸው ቋሚ ምስክሮች ኾነው እንዲያዘክሯቸው ለማስቻል ነው፡፡

*የፍጥረታትን የመኖር መብት ለማክበር፦* ዕፅዋትም ኾኑ እንስሳት እንዲሁም ሌሎች ፍጥረታት በፍጥረት ጊዜ እንደ ሰው የመፈጠሪያ ዕለት ተሰጥቷቸው የተፈጠሩ መኾኑ - ምንም እንኳን ለሰው የተፈጠሩ ቢኾኑም እስከ ዐለም ፍጻሜ የመኖር መብት እንዳላቸው ያጠይቃል፡፡ ይልቁንም ለእርሱ ደኅንነትና ምቾት የተፈጠሩለት የሰው ልጅ የመጥፋት አደጋ እንዳያደርስባቸው የሥነ ሕሊና (moral) ግዴታ እንዳለበት ለማዘከር ነው፡፡

*ቅርስ በመኾናቸው፦* በእነዚህ ዛፎች/ደኖች ጥላዎች ሥር ብዙ ቅዱሳን አባቶችና እናቶች በቅድስና ጸልየውባቸዋል፤ በኋላም አጽማቸው በሥራቸው አርፎባቸዋል ናቸው፡፡ ይኽም ደኖቹን ቅርስ ያደርጋቸዋል፡፡

እንዲኹም በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በተአምረ ማርያም፣ በገድላትና በድርሳናት የዛፎች ጠቀሜታና አስፈላጊነት በተደጋጋሚ ተጽፎ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት ዛፎችና ሌሎች ፍጥረታት ክብርና ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ነገር ግን የትኛውም ዛፍ ወይም ፍጥረት እንዲመለክ ወይም የአምልኮ ሥርዐት እንዲፈጸምለት ቤተ ክርስቲያን አታስተምርም፡፡ በመኾኑም የቤተ ክርስቲያኗ የብዝኀ ሕይወትና ደን ጥበቃ ልምድና አስተምህሮ ከሣይንሳዊና ሥነ ምኅዳራዊ (Ecological) መርሕ ጋር የተጣጣመ፣ ለጥናትና ንጽጽርም ሰፊ ዕድል የሰጠና የፈጠረ ነው፡፡

---

[3] ዘፍ ፪፥፰-፲

[4] ዘፍ ፪፣ ፲፭

## ፫. የአድባራትና ገዳማት ደኖች ምን ጥቅም ይሰጣሉ? (በሣይንስ እይታ)

**ደን/ጫካ፡** የተለያዩ የእንጨትነት ባሕርይ ያላቸው ቋሚ ዕፅዋት/ዛፎች ተሰባስበው ከግማሽ ሄክታር በላይ የኾነ መሬትን በመሸፈንና አጠቃላይ የቅርንጫፍ ጥላቸው የሰፈሩበትን መሬት ቢያንስ ፲ በመቶውንና ከዚያ በላይ ሸፍነው ሲገኙ ነው፡፡[5] በአድባራትና ገዳማት ተጠብቀው የቆዩ ደኖች አብዛኛዎቹ ከግማሽ ሄክታር በላይ የሚኾኑና የቅርንጫፍ ጥግግታቸው መጠንም በአማካይ ከ፳ በመቶ በላይ በመኾኑ በኪናዊ (technic) እና ሣይንሳዊ ትንታኔ ረገድ ደን ተብለው ሊጠሩ ወይም ከደን ሊመደቡ ይችላሉ፡፡[6]

በአድባራትና ገዳማት ተጠብቀው የቆዩ ደኖች ማንኛውም ደን የሚያበረክተውን የምርትና የአካባቢ ጥበቃ ጥቅምና አገልግሎት የሚሰጡ ከመኾናቸው በተጨማሪ ካላቸው ልዩ ባሕርይ የተነሣ ልዩ ጥቅምና አገልግሎትም ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ደኖች የቀድሞው የተፈጥሮ ደኖች ቅሪት በመኾናቸው በውስጣቸው ተጠብቀው የሚገኙትም ዕፅዋት፣ እንስሳትና ረቂቅ ተዋሕስያን እስከነመስተጋብራቸው ሀገር በቀል በመኾናቸው ከብዝኀ ሕይወትና ሥነ ምኅዳር ሚዛን ጥበቃ አኳያ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥቅሞች ይሰጣሉ፡፡

ሀ. ብዝኀ ሕይወትን ለመጠበቅ ምቹ ዕድልና አጋጣሚ ፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በ፳፰ አድባራትና ገዳማት ላይ በተደረገ ጥናት ከ፻፷፰ በላይ ሀገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎች መኖራቸው ተረጋግጧል (አባሪውን ይመልከቱ)፡፡ እንዲሁም በርካታ አጥቢ እንስሳት፣ አዕዋፍ፣ በደረት ተሳቢና አነስተኛ ነፍሳት ተጠልለው የሚኖሩ መኾኑ ታውቋል፡፡[7] ከእነዚህ ዝርያዎች ውስጥ አብዛኞቹ ከሀገሪቱ ገጸ ምድር ላይ የጠፉና እየጠፉ ያሉ መኾኑንም ልብ ይሏል፡፡

ለ. በመስክ ላይ ለሚደረግ የተግባር ትምህርትና ምርምር እጅግ ምቹ በመኾናቸው በሥነ ሕይወት (Biology)፣ ሥነ ምኅዳር (Ecology)፤ ደን ሣይንስ (Forestry)፤ መድኀኒት ቅመማ (Pharmacology)፤ ሥነ ማኅበረሰብና አንትሮፓሎጂ (Sociology and Anthropology)፤ ተፈጥሮ ታሪክና ሥነ ዕፅዋት (History and Planetology) መስክ ለሚደረግ ጥናት እጅግ ተመራጭ መሆናቸው ግልጽ ሆኗል፡፡

ሐ. የቀድሞውን የሀገሪቱን የሥነ ምኅዳር ገጽታ ለማጥናትና ወደፊትም መልሶ ለማልማት እንደ መነሻ ሥነ ምኅዳር (Reference Eco-system and Stepping Stones) የዘር፣ የዘረመል፣ የጀርም ፕላዝም ምንጭ በመኾን ያገለግላሉ እያገለገሉም ይገኛሉ፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት በማእከላዊና ሰሜናዊ ኢትዮጵያ በሕዝቡና በመንግሥት እየተካሄደ ያለውን የተጎዳ አካባቢን የማዳንና የቀድሞውን ሥነ ምኅዳር የመመለስ ጥረት በተፈጥሮ መስተጋብርና ቁርኝት የዘርና የአሰራጮች ምንጭ በመኾን የማገገም ኺደቱን እየገሩና እየመሩ መኾናቸውን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ቅሪት ደኖች የተፈጥሮ ገጽታን ለመለወጥ በመነሻ ነጥብነትና በማስነሻ ሞተርነት የመጨረሻ ዕድል በመኾን እያገለገሉ ይገኛሉ (ምስል ፪ን ይመለከቱ)፡፡[8፣9]

---

[5] FAO. Forestry Department. Global Forestry Resource Assessment: Terms and Definition. (Rome 2010).

[6] Alemayehu Wassie, Frank J. Sterck, and Frans Bongers‖ *Species and structural composition of church forests in a fragmented landscape of Northern Ethiopia*. Journal of Vegetation Science 21 (2010), pp938-948.

[7] Sergey G. Ermilov, Neville N. Winchester, Margaret M. Lowman & Alemayehu Wassie. *Two new species of oribatid mites (Acari: Oribatida) from Ethiopia, including a key to species of Pilobatella*. Systematic & Applied Acarology 17(3) ( 2012).

[8] Alemayehu Wassie, Demel Teketay and N. Powell, *Church forests provide clues to restoring ecosystems in the degraded highlands of Northern Ethiopia*. Ecological Restoration 23 (2) (2005b).

[9] Bongers, F., Alemayehu Wassie, F. J. Sterck, T. Bekele and D. Teketay. *Ecological restoration and church forests in northern Ethiopia*. Journal of the Drylands 1 (2006), pp35-45.




ምሥል ፪. የቤተ ክርስቲያን ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች የተጎዳን አካባቢ እንዲያገግም ሲያግዙ (ደቡብ ጎንደር)

## ፬. የአድባራትና ገዳማት ደኖች ምን ወቅታዊ ችግሮችና ፈተናዎች አሉባቸው?

እነዚህ በቀደሙ ቅዱሳን አባቶችና እናቶች አርቆ አስተዋይነትና አደራ ጠባቂነት ዘመናትን ተሻግረው ከዚህ ትውልድ የደረሱት ደኖች በአሁኑ ዘመንና ወቅት ለፈተና ተጋልጠዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የተጋለጡባቸው ፈተናዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የሃይማኖት ትሩፋትና የሥነ ሕሊና (moral) ሕግ የማይገዛቸው ራስ ወዳድ ግለሰቦች ለእርሻና ለመኖሪያ ቀስ በቀስ የደኖችን ድንበር በመጋፋታቸው አልፎ አልፎም ነባር ዛፎችን በመቁረጣቸውና በእሳት በማያያዛቸው የደኑ ይዞታ መጠን እንዲቀንስ አድርገዋል፡፡

ለ. በሰሜናዊው የሀገሪቱ ክፍል ያለው ልቅ የእንስሳት ግጦሽ ሥርዐት እንስሳት ወደ ደኖቹ እንዲገቡ በማደፋፈሩ የዕፅዋት ቡቃያ እንዲጠፉ፣ መሬቱም እንዲጠቀጠቅና እንዲጠብቅ በማድረግ የዛፍ ብቅለትን አግዷል፡፡ ይኸም ሁኔታ የዕፅዋቱን የመራባትና ራስን የመተካት ኺደት አቋርጧል፡፡[10]

ሐ. የቤተ ክርስቲያኑን አስተምህሮ ጠንቅቀው የማያውቁ አንዳንድ የሰበካ ጉባኤ አባላት የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ በማደስ ሽፋን የተፈጥሮ ሀብቱን (ነባር ዕፅዋቱን) ከሚፈለገው በላይ በመቁረጣቸው የደኑ ይዞታ እንዲመናመን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

መ. በቤተ ክርስቲያኗ ሥርዐትና እምነት ተቀባይነት የሌለውና ከውጭ ሀገር አብያተ እምነቶች የተኮረጀው የመቃብር ላይ ሐውልትና ቤት ግንባታ የደኑን ይዞታ እጅግ አድርጐ የሚያራቁተው ኾኖ ተገኝቷል፡፡ ኾኖም ግን እውነተኛውና ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያኗ አስተምሮ ‹‹አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ›› እንደተባለ ደሀም ቢሆን ባለጸጋ፣ ያልተማረም ቢኾን የተማረ፣ ሴትም ብትሆን ወንድ፣ ሕፃንም ቢኾን ዐዋቂ ኹሉንም በአንድ መልክ በተቀደሰው ዐጸድ ውስጥ በመቅበር ለምልክት እላዩ ላይ የዕፅዋት ችግኝ ይተከልበታል ወይም በተፈጥሮ ይበቅልበታል፡፡ ከሚያድጉት ዕፅዋት ሥርም ቅዱሳን፣ ስውራና መናንያን ይጸልዩበታል፡፡ የክርስቲያን ማስታወሻውና መታሰቢያው መልካም ተግባሩና ልምላሜ ባለው ዕፅዋት እንጂ ግዑዝ ክቡድ በኾነው በእብነ በረድና በግንብ ክምር አለመኾኑን የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ያስገነዝባሉ፡፡ ቀድሞውኑ መቃብርን የሚያሣምሩ ግብዝ አይሁድ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መኾናቸውን ለማጠየቅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ይህንን የግብዝነት ተግባር በሚከተለው ኀይለ ቃል ገስጾታል፡፡

> *‹‹በውጫቸዉ አምረው የሚታዩ በውስጣቸዉ ግን የሙታን አጥንት ርኵሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን የምትመስሉ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳዊያን ወዮላችሁ፡፡ ››* ማቴ ፳፫፥ ፳፯[11]

> *‹‹የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ የጻድቃንንም መቃብር የምታስጌጡ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳዊያን ወዮላችሁ፡፡››* ማቴ ፳፫፥ ፳፱-፴ [12]

---

[10] Alemayehu Wassie, Frank J. Sterck , Demel Teketay Frans Bongers. *Effects of livestock exclusion on tree regeneration in church forests of Ethiopia*. Forest Ecology and Management 257 (2009), pp.765–772.

[11] በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፳፻ ዐ.ም.

[12] ዝኒ ከማሁ

ከላይ የተገለጹት ዋና ዋና ችግሮች አሁን በአሉበት መጠንና ግፊት ከቀጠሉ የእነዚህ የሀገር ሀብት የኾኑት ብርቅዬ ደኖች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ከምድር ገጽ መጥፋት ይሆናል፡፡[13፣14] የእነዚህ ደኖች መጥፋት ደግሞ ለማእከላዊና ሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍል የብዝኀ ሕይወትና የደን ዘረመል ሀብት የመጨረሻው ተስፋ መጨለምንና እስከ ወዲያኛው ከገጸ ምድር መጥፋትን ያስከትላል፡፡ ስለምን? ሌላ ቦታና አካባቢማ ቀደሞውኑ ጠፍተዋልና!

## ፭. የአድባራትና ገዳማትን ደኖች ለማቆየት ምን ይደረግ?

በቀደሙ ባለቃል ኪዳን አባቶችና እናቶች ተጋድሎ እዚህ ዘመን የደረሱትን ሀብቶች ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚከተሉትን ነጥቦች መተግበር መልካም ይኾናል፡፡

ሀ. የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተገቢውን የሕግ ከለላና የበጀት ድጎማ በማድረግ በሀገሪቱም ኾነ በዐለም ዐቀፍ ደረጃ ጠቀሜታቸው እጅግ ከፍተኛ የኾኑትን እነዚህን ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች እንዲታደጉ ትኩረት መስጠት፡፡ በተለይም

- የወሰን ክልላቸውን በማመልከት (Land Mark) በደን ይዞታነታቸው እንዲከበሩ የሕግ ድጋፍ ማድረግ (Gazzett)
- እየደረሰባቸው ካለው የእንሰሳት ልቅ ግጦሽ ለመታደግ ዙርያቸውን እንዲታጠሩ ኅብረተሰቡን ማስተባበር (ምሥል ፫ ን ይመልከቱ)



ምሥል ፫. የቤተ ክርስቲያን ቅሬት የተፈጥሮ ደኖች ዙርያቸውን በድንጋይ ካብ ታጥረው

- በዕድሜና በሌሎች ምክንያቶች እራሳቸውን መተካት ያቆሙትን የዕፅዋት ዝርያዎች ችግኝ አፍልቶ መተካት እንዲሁም የዕፅዋቱን ዝርያ በየጊዜው መከታተልና ከተቻለ ዘራቸውን መሰብሰብ ጊዜ የማይሰጣቸው ዋና ዋና የቴክኒክ ድጋፎች ናቸው፡፡

ለ. የዘመናችን የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንትና መምህራን እንደቀደሙት ኹሉ የቤተ ክርስቲያኗን የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ አስተምህሮ (Ecotheology) እንደገና በማሙላትና በማብራራት ለዘመኑ ትውልድ ማስተማር ይገባቸዋል፡፡

[13] Alemayehu Wassie. *Ethiopian Orthodox Church Forests: Opportunities and challenges for Restoration*. (PhD Thesis. Wagningen University the Netherlands, 2007).

[14] Alemayehu Wassie, Frank J. Sterck , Demel Teketay Frans Bongers. *Tree Regeneration in Church Forests of Ethiopia: Effects of Microsites and Management*. BIOTROPICA 41(1) (2009), pp 110–119.

ሐ. በየአድባራቱና ገዳማቱ አቅራቢያ የሚኖሩ ምእመናን እነዚህ ደኖች የሃይማኖታቸውን ጥልቀትና መሠረተ ሰፊነት ማሳያ፣ የፈጣሪ ቃል ኪዳንና የቀደሙ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ታማኝነት መገለጫ መኾናቸውን ዐውቀው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ደኖች በአንድ ወቅት ለሀገርና ለወገን ሲጸልዩ በነበሩ መናንያን የመናንያኑንን አጽም እንባ ያደኑና በውስጣቸውም የመናንያኑን ዐጽም አቅፈው የያዙትን መካነ ዕፅዋት መድፈር ሃይማኖታቸውን ማዋረድና የቅዱሳንንም ቃል ኪዳን ማፍረስ መሆኑን ተገንዝበው ልዩ ክብካቤ እና ርኅራሄ ማድረግ እንዳለባቸው ተገንዝበው መተግበር ይገባቸዋል፡፡

መ. ምእመናን ሙታን ወገኖቻቸውን ለማሰብ መቃብርን በእብነ በረድና በግንብ ከማስጌጥ ይልቅ በጸሎትና በዕፅዋት የተፈጥሮ ውብ ምሥጢር እንዲታሰቡ እንደቀደሙ አባቶችና እናቶች ያለግብዝነት ‹‹አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ›› የሚለውን ሕግ ለመፈጸም ቢበረቱ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ይችላሉ፡፡

ሠ. ዐዳዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች ግንባታዎች ማካሄድ ሲያስፈልግ  ቢቻል በፋብሪካ ውጤቶች ማነጽ ይህ ካልተቻለም ለግንባታው ብቻ የሚያገለግል የተመጠነ የዕፅዋት ቊጥር ቆርጦ መጠቀም ይገባል፡፡ እነዚህን ዕፅዋት እንደ ገቢ ወይም  የገንዘብ ማስገኛ አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡

ረ. ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ለማስገኘትና የደኑን ጥቅም ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የደን ንኡስ ምርትን ማለትም የንብ ርባታን፣ የቅመማ ቅመም፣ የመድኀኒትና ዘር መሰብሰብሰን እንዲሁም የካርቦን ንግድን፣[15፣16] ማበረታታትና ማስፋፋት ተጨማሪ ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ማበረታታትና በዚህ በኩል ልምድ ካላቸው ተቋማት ጋር በትብብር መሥራት ይገባል፡፡

ሰ. ለገቢ ምንጭነት የሚያገለግሉ ፈጣን የኾኑ የውጭ ሀገር ዝርያ ዕፅዋትን ማልማት ከተፈለገ ከሀገር በቀል ዝርያዎች ጋር ሳያሰባጥሩ ራሱን አስችሎ (Compartment) ማልማት ያስፈልጋል፡፡

ሸ. ከእምነቱ ውጭ ያሉ ዜጐችና ወገኖችም እነዚህ ደኖች በባለቤትነት የሚተዳደሩት በቤተ ክርስቲያኗ ቢኾንም የደን ጥቅም ግን በባሕርዩ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ምኅዳራዊ በመኾኑ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚዎች መኾናቸውን ተረድተው የበኩላቸውን በጎ ፈቃድና ትብብር እንዲያደርጉ ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የመፍትሔ ሐሳቦች በተግባር ላይ ማዋል ከተቻለ ከሌሎች ተጨማሪ ጥረቶች ጋር እነዚህን ደኖች ድጋፍና የመነሻ ነጥብ በማድረግ የሀገራችንን  ከፍተኛ ቦታዎች ልምላሜና የደን ሽፋን መመለስ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አሁን ያለው ግዴለሽነት ቀጥሎ ምንም የማናደርግ ከኾነ አሁን እየታየ ያለው ጫና እነዚህን ቅሪት ደኖችም በአጭር ጊዜ ማጣትን ያስከትላል፡፡

እያንዳንዱ ትውልድ በሚቀጥለው ትውልድ የሚታሰብበትን የራሱ የኾነ በጎ አሻራ ጥሎ ያልፋል፡፡ ከአለፈው የተቀበለውን ሲኾን ሲኾን ጨምሮ፣ አስፍቶና አጉልቶ ካልሆነም ደግሞ ቢያንስ እንዳለ ያስተላልፋል፡፡ ስዊድናውያን አንድ ወርቃማ አባባል አላቸው፡፡ *‹‹የተፈጥሮ ሀብት ካለፈው ትውልድ የተበደርነው ሲኾን በአግባቡ ተጠቅመን ለሚቀጥለው ትውልድ ከነወለዱ የምናስተላልፈው ዕዳ ነው››* ይላል፡፡ ይህ ትውልድ ዕዳውን በልቶ ተጨማሪ ዕዳ ለሚቀጥለው ትውልድ ቢያስተላለፍ በምድር የሥነ ሕሊና ኪሣራ በሰማይ አምላክ ፊትም እምነት ማጉደል ይሆንበታል፡፡

[15] Tulu Tolla , Mekuria Argaw and Zewdu Eshetu. (Role of Trees in Churches Compound for Carbon Emission Reduction, Journal of Ethiopian  Church Studies. No 2 (PP125-142).2012

[16] Catherine l Cardelús, Margaret Lowman, Alemayehu Wassie.2012. Uniting Church and Science for Conservation. SCIENCE VOL 335.

## አባሪ

**በደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን የሚገኙና ለናሙና ተመርጠው የተጠኑ የኢብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የተፈጥሮ ደንና ብዝኀ ሕይወት ጥብቅ ሥፍራዎች**[17]

| ተ.ቍ | ስም | ወረዳ | የደን ስፋት በሄክታር | የእንጨትነት ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት ዝርያ ብዛት (Woody Species) |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | መካነ ሰማዕታት ገላውዴዎስ | ደራ | ፯ | ፶፪ |
| ፪ | አዲያመ ርዳኖስ ወንቀሽት ገብርኤል | ደራ | ፱ | ፷፰ |
| ፫ | ገዳመ ቆራጣ ወለተ ጴጥሮስ | ደራ | ፶፰ | ፰ |
| ፬ | ደብረ ምሕረት ዛራ ሚካኤል | ደራ | ፰ | ፳፱ |
| ፭ | ገዳመ እማሸንኮር ጊዮርጊስ | ደራ | ፫ | ፵፰ |
| ፮ | ደብረ በረከት ወጂ አቡነ አረጋዊ | ፎገራ | ፳፪ | ፵፱ |
| ፯ | ደብረ ምሕረት ዐለም በር ኪዳነ ምሕረት | ፎገራ | ፲፬ | ፵፯ |
| ፰ | ፈብረ ልዑል kር ሚካኤል | ፎገራ | ፫ | ፵፬ |
| ፱ | ድድም ጽዮን | ፋርጣ | ፵፮ | ፳፪ |
| ፲ | ጭጎተ ገነት ደብረ ሲና ማርያም | ፋርጣ | ፲፩ | ፵፬ |
| ፲፩ | ደብረ ሰላም ዋሒር እስጢፋኖስ | ፋርጣ | ፰ | ፵ |
| ፲፪ | ደብረ ጎሩያን ጎሩይ ጊዮርጊስ | ፋርጣ | ፬ | ፵፩ |
| ፲፫ | ደብረ መዳልው ደንጎልት ማርያም | እስቴ | ፳፭ | ፵፮ |
| ፲፬ | ሞሻ ማርያም | እስቴ | ፯ | ፶፫ |
| ፲፭ | ደብረ ዛጉዋ ሩፋኤል | እስቴ | ፮ | ፵፫ |
| ፲፮ | ምዕራፈ ቅዱሳን ገዳም ሥላሴ | ስማዳ | ፲፭ | ፷፬ |
| ፲፯ | ደብረ መንክራት ደደር ሚካኤል | ስማዳ | ፲፬ | ፳፪ |
| ፲፰ | ገዳመ መቅደሰ ማርያም | ስማዳ | ፬ | ፵፫ |

[17] Alemayehu Wassie, *Ethiopian Orthodox Church Forests: Opportunities and challenges for Restoration*. (PhD Thesis, Wagningen University the Netherlands, 2007).

| ተ. ቁ | ስም | ወረዳ | የደን ስፋት በሄክታር | የእንጨትነት ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት ዝርያ ብዛት (Woody Species) |
|---|---|---|---|---|
| ፲፱ | መንበረ ልዑል አስቻ ሚካኤል | ላይ ጋይንት | ፩ | ፳፪ |
| ፳ | ገዳመ አሶሊት ሚካኤል | ታች ጋይንት | ፯ | ፴፯ |
| ፳፩ | ደብረ እንዝጥ ቁስቋም | ታች ጋይንት | ፮ | ፳፮ |
| ፳፪ | ደብረ ጣዕም ሻሞ መድኀኔዐለም | ሊቦ ከምከም | ፲ | ፶፰ |
| ፳፫ | ገዳመ ማንቶገራ እስጢፋኖስ | ሊቦ ከምከም | ፭ | ፵፬ |
| ፳፬ | ወንበሮች ኪዳነ ምሕረት | እብናት | ፴፭ | ፲፭ |
| ፳፭ | አበገልዲ ሚካኤል | እብናት | ፲፬ | ፲፱ |
| ፳፮ | አምስተያ የአንድነት ገዳም | እብናት | ፳፪ | ፵፩ |
| ፳፯ | ግብጻዊት ማርያም | እብናት | ፰ | ፴፭ |
| ፳፰ | ገዳመ ጉናጉና ጊዮርጊስ | እብናት | ፮ | ፴፬ |